አብይ የቀትር ጅብ

በዛሬው እለት የኦሮሙማው ገዥ የአብይ አህመድ ሰራዊት ኢትዮጵያውያን ላይ የፈፀመው ግፍ ታሪክ ይቅር የማይለው ነው። የአድዋ ድልን 127ኛ ዓመት በዓል ለማክበር ወጥተው በግፍ መስዋዕት ለሆኑትና በቅዱስ ቢዮርጊስ ክብረ በዐል በቤተክርስቲያን ግቢ በአስለቃሽ ጭስ ታፍነው ለተጎዱት፣ ካህናትና ምዕመናን ወገኖቼ በደረሰባቸው ሁሉ በጣም አዝኛለሁ። ለነገሩ የኦሮሙማው መንግሥት ተብዬው " ክፉ ጎረቤት እቃ ያስገዛል" እንዲሉ አማራን ሲያሳድዱ አማራ፣ ኦርቶዶክስን ሲያሳድዱ እውነተኛ አማኝ እንዳደረገን ይታወቃል። አሁን ደግሞ በእምዬ ምኒሊክ ላይ ያላቸው ጥላቻ ከፍተኛ መሆኑ ለእኛ በእምዬ ምኒሊክና በአድዋ ጀግኞች በፍቅር ላይ ፍቅር፣ በአክብሮት ላይ አክብሮት እንድንጨምር አድርጎናል። ዛሬ በአረመኔው አገዛዝ ደማችሁ የፈሰሰው ደማችሁ በከንቱ ፈሶ አይቀርም። ትግላችን እስከነፃነት ይቀጥላል።

እምዬ ምኒሊክ፣ የአድዋው አባት

የዘላለም ኩራት፣ የድል መሠረት

በማስተዋል መሪ፣ የጥበብ አባት

ህያው ታሪክ ያለህ፣ ደግሞ የሚያሸት።

የባንዳ ሰቀቀን፣ ሁሌም ባለግርማ

ማንም አያወርድህ፣ ከከፍታ ማማ።

ኢትዮጵያን ለማጥፋት፣ እየተነሳሳ

በሰበብ ባስባቡ፣ ስምህን ሊያስረሳ

ሞክሮ ነበረ፣ ሆኖም አልተሳካ።

አገርህን ወሮ፣ አብይ የቀትር ጅብ

በአሳሳች ምላሱ፣ የሆነው እባብ።

ህሊና ቢስ አውሬ፣ ቢያተረማምስ

የድል አድራጊ ልጅ፣ አንጀት የሚያርስ

እንደሆን አይርሱ፣ እስከዛው ድረስ።

ዘውዲቱ የማነ

2023-03-02